# ህወሓት/ወያነ እና የትግራይ ሕዝብ

ከነብዩ ያሬድ

## መግቢያ

የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማ የትግራይ ሕዝብና የተሓህት/ህወሓትን የግኑኝነት ታሪክና ወቅታዊ ሁኔታ እጅግ በጣም በአጭሩ መግለጽ ነው። የዚህ ፅሁፍ ፀሓፊ የተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ወዳጅና ጠላትን የመለየት ብዥታ ሰፍኖ ይገኛል ብሎ ያምናል። ይህንን ብዥታ ማጥራት ደግሞ የአገራዊው ዴሞክራሲያዊ የአንድነት ትግሉ ሀሁ ነው ብሎ ያምናል። ስለዚህ ይህ ጽሁፍ የትግራይ ሕዝብና የተሓህት/ህወሓትን ታሪካዊና ወቅታዊ ግኑኝነት እጅግ አጭር በሆነ መንገድ በመግለጽ ወዳጅና ጠላትን በመለየት ረገድ አስተዋፅዖ ለማድረግ ታስቦ የቀረበ ነው። ይህ ጉዳይ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በርካታ ጦማሮች ሊወጣው የሚችል በመሆኑ በዚህ አጭር፣ አጠቃላይና ቀላል አቀራረብ ይሸፈናል የሚል ግምት በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ዘንድ የለም።

ተሓህት/ወያነ የአገሪቱን በትረ-መንግሥት ወሮ ከያዘ ሩብ ምእተ-ዓመት ሊደፍን ነው። በነዚህ ሁሉ ዓመታት ሲለው በዴሞክራሲ ሥም እያላገጠ፤ ሲያሰኘው ደግሞ በፌዴራል ፖሊስና በጦር ኃይል እየደፈጠጠ ሲገዛ ኖሩዋል። የአገዛዙን ኢ-ዴሞክራሲያዊነት ለመገንዘብና እርሱ የሚመርጠው የፖለቲካ ቧልት ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን እውን ለማድረግ የሚበጅ ሁነኛ የትግል ስልት መርጦ ለመገኘት የታለፈው ጊዜ እጅግ በጣም ከበቂ በላይ ነው። አለመታደል ሆኖ ግን አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶች ከመጃጃል ለመላቀቅ ብቃት ሳያገኙ ቀርተው ይሁን ወይም አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንዲሉ ሆኖ የገዢው ቡድን የምርጫ ድራማ አዳማቂና ማላገጫ ከመሆን የዘለለ እርባና ያለው ነገር ሳይሰሩ ዘልቀዉታል። በዚህ ሳቢያ ጐሳ-በቀሉ ፋሺስታዊ አገዛዝ በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን በተቃዋሚው ድክመት ሳቢያ ካሰበው በላይ በሥልጣን ኳርቻ ላይ ፍጢጥ እንዳለ ለመከረም የታደለበት ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ነው የሚገኘው።

ስለ ተሓህት/ወያነ ማንነትና ምንነት ገና ድርጅቱ ጫካ ሳለ የተነገረና የታወቀ ጉዳይ ነው። ድርጅቱ ሥልጣን ከያዘ በኋላም በወታደር ኃይል እየደፈጠጠ፣ በግፍ የንፁሃንን ሕይወት እየቀጠፈና ለመብታቸው የሚታገሉ ዜጐችን እንበለ ፍትህ ዘብጢያ እያወረደ እውነተኛ ባህርዩ በገቢር አሳውቆናል። በተለያየ ደረጃ የሥርዓቱ አገልጋይ ሆነው አብረው ሲወቅጡን የከረሙትም በሆነ ምክንያት ሥርዓቱን

ሲለዩ ስለ ሥርዓቱ ግምነት መስክረውልናል። የሥርዓቱ ቁንጮ የነበሩት ሟቹ ሰውዬም ጣታችን፣ እጃችን ወዘተ ... እንደሚቆርጡን እኛኝ እስኪለን ድረስ እየዛቱና በገቢርም እያሳዩን ለአገሪቱና ለሕዝቧ ያላቸውን ንቀትና ጥላቻ አሳይተውናል። ይህ ሁሉ ግን የሚገባንም የሚሰማንም አንመስልም። አገዛዙ እራሱ 'እኔ ግም ሥርዓት ስለሆንኩኝ መወገድ ይገባኛልና ይኸው እራሴን በራሴ መነገልኩላችሁ' እስኪለን የምንጠብቅ ነው የምንመስል። ይህ ደግሞ ሲያምረን ይቀራል እንጂ መቼም ቢሆን የሚፈጸም አይደለም።

ካለፈው የቅርብ ጊዜ የአገራችን ታሪክ ልንማር እንደምንችለው አገዛዞች በሕዝብ ቢጠሉም፣ ባይፈለጉም ራሳቸውን በራሳቸው ሲፈነግሉ ወይም ተነው ሲጠፉ አልታዩም። ለምሳሌ በየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት የተገረሰሰው ዐፄያዊው ሥርዓት ተዳክሞና አብቅቶለት ሳለ ገፌ አሻ እንጂ ራሱን በራሱ አልፈነገለም። ተሓህት/ወያነ ገረሰስኩት፣ አሸነፍኩት፣ ቅብርትስ እያለ የሚመጻደቅብን የኢሥፓ/ኢህዴሪ ሥርዓትም ቢሆን ሕዝቡ ፊት ነስቶት፣ ድጋፍ ነጥፎበት፣ ውስጡ ተቦርቡሮና በቁሙ ደርቆ እያለ ራሱን በራሱ አልመነገለም፤ ሎተሪ በወጣለት ተሓህት/ወያነ እስኪተካ ጠበቀ እንጂ። የተሓህት/ወያነ ፋሺስታዊ መንደርተኛ ቡድንም ከእርሱ በፊት እንደነበሩቱ አስወጋጅ ኃይል እስኪያገኝ ድረስ ቀርንቶም ቢሆን ባለበት መገኘቱ የማይቀር ነው። ሁኔታው የሚጠይቀው ይህንን ሆኖ ሳለ ተቃዋሚ ነን ባዮች ግን አሁንም ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን የሚያባክኑት ከምጽአተ-ተሓህት/ወያነ ዋዜማ አንስቶ ታውቆ ያደረውን የአገዛዙን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነት፣ ቤተ-ሰባዊነትና መንደርተኛነት፣ ሙሰኛነት፣ ወዘተረፈ ... በመደስኮር ላይ ነው። ብዙ ተቃዋሚ ነን ባይ ወገኖች የድግምት ነገር እስኪያስመስልባቸው ድረስ ቁርጠላቸው ከእንደዚህ ዓይነት አባዜ ለመውጣትና ከአገዛዙ ጋር የሚያደርጉትን ድሪያ ለማቆም በቅተው አይታዩም።

እርግጥ ነው የተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ጥራት ጐድሎ፣ የእንክርዳዱም የስንዴውም አንድላይ መርመስመስ አብዝቶ የሚታይ በመሆኑ ተቃዋሚውን ኃይል በአንድ የወል ሥም በጥቅሉ በተቃዋሚነት ብቻ ፈርጆ ማየት አይቻልም። አይገባምም። ለከፊሉ የተቃዋሚው ጐራ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማምጣት፣ አገርን ከጥፋት መታደግ፣ ሕዝብን ከአረመኔአዊ ጐሰኛ አገዛዝና ከድኅነት አረንቋ ነፃ ማውጣት የትግሉ ማዕከል ነው። ለሥራ-አጥ ፖለቲከኞች ደግሞ የአሥሪና ሠራተኛ መገናኛ ማዕከል ነው። ለሌሎቹ ደግሞ የጡረታ ዘመን ጊዜ ማሳለፊያና ዝና መሸመቻ ገበያ ነው። በእርግጥ ፀረ-አገዛዙ ትግል ለአንዳንዶቹ የጡረታ ጊዜ ማሳለፊያ ነው ሲባል፤ ትግሉ የወጣቶችና የጎልማሶች ብቻ ነው የሚለውን ደካማና ከፋፋይ ቅኝት ለማቀንቀን ወይም ለመደገፍ አይደለም። የሕዝባቸው መከራና የአገራቸው ህልውና አደጋ ላይ ወድቆ መገኘቱ ሠላም ነስቷቸው፤ በማረፊያ ጊዜአቸው ለሕዝባቸውና ለአገራቸው ከልብ ተቆርቁረው ሲታገሉ መከራ የተቀበሉ፣ ለፋሺስታዊ ሥርዓት ጥቃት የተዳረጉና አሁንም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆነው የሚታገሉ አዛውንቶች መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር

ነው። መጥቀስ የተፈለጋው እንዲህ ያልሆኑትን ነው። ነገር ጠጠር ሲልና የሚያስጠጋ ሲገኝ ሸብረክ ብለው ከሞሰቢቱ ስር የሚነጠፉ፤ አገዛዞቹ ደከመው ሲታዩዋቸውና አስጠጊ ሲታጣ ደግሞ የሕዝብ መብት አስከባሪ ፊታውራሪዎች ሆነው የሚያደናግሩትን ነው። ያም ሆነ ይህ ግን የተቃዋሚው ጐራ ጥራት ነጥፎበታል። እውነተኛ ለሕዝብ መብት የሚታገሉ ኃይሎች፣ የምርጫ ሰሞን አውደልዳዮችና ፍርፋሪ ለቃሚ የፖለቲካ ሥራ-አጦች አንድ ላይ የሚርመሰመሱበት ዝብርቅርቁ የወጣ የገበያ ቦታ ሆኖ ነው የሚታየው። ድክመት ጠርንቶ ይዞትና ጨለምተኛነት አጥልሎበትም ተስፋን አምካኝ ሆኗል። በዚሁ ጐራ ውስጥ የሚርመሰመሱት አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ነን ባይ ስብስቦች ገዢ ቡድኑ ሲያጕረጠርጥባቸው ጭራቸውን ቆልፈው የሚሸመጥጡና ላላጠፉት ጥፋት ምህረትን የሚማጸኑ የአገዛዙ አሻንጉሊቶችና ተስፋ አስቆርጭ የሕዝብ ማፈሪያዎች ሆነው ነው የሚታዩት። የተሻለ ነው ከተባለም ከድምፅ መስጠቱ በፊት ድምፁ ተቆጥሮ ባለቀለት፣ ቢሸነፍም ባይሸነፍም አሸናፊው ገዢ ቡድኑ በሆነበት ምርጫ ለመሳተፍ እየተሽቀዳደሙ ከምርጫው በፊት ተሸንፈው ለውድድር የሚቀርቡ ለአገዛዙ የምርጫ ቧልት ሽፋን ሰጪ ከመሆን አያልፉም። ጥቂት የጸና አቋም ይዘው የሚታገሉ ግለሰቦች በየድርጅቶቹ ሊገኙ መቻላቸው አሌ የማይባል ቢሆንም የአብላጫው የህገ-ደደቢት አክባሪ ተቃዋሚዎች ባህርይ ግን ከዚህ ብዙ ርቆ የሚታይ አይደለም።

የትግሉ በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ እየዳኸ መገኘት የብዙዎችን ስሜት መጐዳቱ የማይቀር ጉዳይ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ምክንያትም የተለያዩ አመለካከቶች ሲሰነዘሩ ይስተዋላል። አንዳንዴ ሰዎች ተቃዋሚ ድርጅቶችን 'መተባበር የማይችሉ፣ ደካሞች፣ ወዘተ …' እያሉ ሲያብጠለጥሉና ሲተቹ ይሰማል። 'ምን የረባ ተቃዋሚ አለ፣ ዝም ብሎ የራስን ሕይወት መኖር ይሻላል' ዓይነት ምክንያትም ሲሰጥ ይደመጣል። የአባባሎቹ እድምታ በደፈናውና በጥቅል ሳይሆን ከባዩ ማንነት ጋር ተቆራኝቶ ሊፈተሽ ይገባል። ለትግሉ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል አስተዋጽዖ እያበረከቱ የሚጠብቁት ውጤት ወይም መሆን ያለበት ነገር ሆኖ ሳያዩ ሲቀሩ እንዲያ የሚሉ ወገኖች አሉ፤ አይፈረድባቸውም። ለአስረሽ ምችውና ለግል ጥቅም ሲሆን ከተፎዎች፤ ለሕዝብና ለአገር ጉዳይ ሲሆን ደግሞ የውኃ ሽታ ሆነው የሚገኙትም ወሬ ለመጠረቅና የሞራል ንቅዘታቸውን ለመሸፈን ሲሉ እንዲያ ይላሉ። የዓላማ ጉዳይ ሆኖባቸው የአገዛዙ ስውር መልዕክተኞችም ሕዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥና የተቃዋሚ ጐራውን ለማዳከም እንዲያ ይላሉ። በርግጥ ዕውነተኛ ያልሆኑ አላጋጭ ግለሰቦችና ስብስቦች በተቃዋሚው ሠፈር እንዳሉ፣ እያውደለደሉና ለመናኛ ጥቅም ሲሉ ትግሉን እንደሚያዳክሙ መካድ አይቻልም። ያም ተባለ ይህ ግን የተቃዋሚ ድርጅቶች ድክመትም ሆነ ጥንካሬ የሕዝቡ ድክመትና ጥንካሬ መገለጫ ከመሆን አያልፍም። ወዳጅና ጠላቱን አነጥሮ፤ የማንም ሰሞነኛ አውደልዳይ ማላገጫ ከመሆን ራሱን ታድጐ፤ እውነተኛ ተቃዋሚዎችን አቅፎና ደግፎ ማጠናከር የሕዝቡ ድርሻ ነው። እንዲያ ሲሆን ብቻ ነው የተቃዋሚዎች ክንድ ፈርጥሞ የሕዝቡን ትግል በአግባቡ ለመምራት አቅምና ብቃት የሚኖረውና ይህንን ጐሳ-በቀል ፋሺስታዊ ቡድን ጨርሶ እንዲወገድ ለማድረግ የሚችለው።

ሕዝቡ ለመጣው ሁሉ ልቡንና ኪሱን በርግዶና የጉዳዩ ባለቤትነቱንም አሳልፎ ሰጥቶ መጠቀሚያና መቀለጃ ሆኖ ከተገኘ ግን እውነተኛ ተቃዋሚዎች ሊዳከሙና ትግሉ ሊራዘም፣ እንዲያም ሲል ሊመነምን የግድ ነው። ልብ እንበል! ሕዝባዊው የትግል ጐራ ስንቶቹን አለሌዎችን ነው ያስተናገደው? ለስንቶቹ ነው ድርጐ የተሰፈረው? ስንቶቹ ናቸው ጦራችን አዲስ አበባን ከቧል ብለው ያላገጡብን? እነ ክህደቱ፣ እነ ምህረት ተመጽዋቾ ተንበርካኪዎች፣ እነ ሲያቃጥል በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ መንታፊዎች፣ ስንትና ስንቱ ነው በሕዝቡ የቀለደው?!

በመሠረቱ በትግሉ ውስጥ ወሳኙ ጥያቄ የሕዝቡ ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ፣ አላጋጩና የምር ታጋዩን አንጓሎ፣ ጥንካሬና ድክመቱን መዝኖ ጉዞውን እስከመጨረሻው ለመጓዝና ትግሉ የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅቶ መነሳት ነው። የወጣቱ ትውልድም ራሱን በዕውቀት አንፆ፣ የአገሩን እውነተኛ ታሪክ አውቆና ታሪኩ የተሠራበትን ወቅትና ሁኔታ ተገንዝቦ፣ ከጠባብ መንደርተኛ አስተሳሰብና ጨለምተኛነት ራሱን አፅድቶ፣ የቀደምት ትውልድን አገራዊ ተጋድሎና ጀግነነትን ወርሶና አድሶ መገኘትም ሌላኛው ለዴሞክራሲያዊ ትግሉ መስመር ወሳኝነት አለው። በዚህ ረገድ መረጃ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው። የሕዝብን ሁለንተናዊ መብት ለማስከበርና የአገር አንድነትን ከጐሳ-በቀሉ ፋሽስታዊ ቡድኑና ጋሻ ጃግሬዎቹ ጥቃት ለማዳን የሚታገሉ ቁርጠኛ ታጋዮች ካሉባቸው ግዙፍ ሥራዎች መካከል አንዱ እውነተኛው ታሪክና ተረት-ተረቱ ነጥሮ እንዳይታይ የጋረደውን ጉም መግለጥ ነው።

በዛሬ ወቅት በተሓህት/ወያነ የአገዛዝ ዘመን ተፈጥረው ጉልቻ ለመመስረት ለበቁ ዜጎች ታሪክ ተብሎ የሚነገራቸው መርዘኛ ተረት-ተረትና የውሸት ታሪክ ነው። በኢትዮጵያዊያን መካከል ያለውን ለዘመናት የተገነባውን አብሮነት ለማዳከምና የተለያየ ማንነት ለመፍጠር በዚህ ጐሳ-በቀል ፋሺስታዊ ቡድን እየተፈፀመ ያለው መርዘኛ ተግባር በጣም አደገኛ ነው። ስለዚህም፤ የእንደነ አቶ መለስ ዜናዊ የመሳሰሉት የባንዳ ቤተሰቦች ባያደርጉትም፤ ትላንት የየቤተሰቡ ተግባር የነበረው የኢትዮጵያ ምንነትና ማንነት የማስረዳትና ህቡር ታሪኳን የማስተማር ተግባር የፖለቲካ አጀንዳ ሆኖ ለማየት የተገደድንበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ይህ ፀረ-አገር አገዛዝ ዓላማው እየሰመረለት ታሪክ ሁሉ፤ ያውም የጐጥ ታሪኮች ከሱ የጀመሩ እስኪመስሉ ድረስ እየተበጁ ነው። ይህ ስሌት ደግሞ ከመቶ ዓመትም በጣም፣ በጣም ያነሰ ነው። በተለያየ አጋጣሚ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ የትግራይ ክፍለ-ሀገር ተወላጅ ወጣቶችና ጐልማሶች በየዋህነት የዚህ ጐሳ-በቀል ፋሺስታዊ ቡድን አፍዝዝ አደንዝዝ ፕሮፓጋንዳ ግዳይ ሆነው የተሳሳተ ተረት-ተረት ሲያስተጋቡ ይስተዋላል። እነዚህ ወጣቶችና ጐልማሶች ከወያነ በፊት አማራ የሚባል ብሔር ገዥ እንደነበረና በተሓህት/ወያነ እንደተወገደ ያምናሉ። የደርግና የኢሠፓ/ኢህዴሪ መንግሥት ትግርኛ ተናጋሪውን ሕዝብ ብቻ ለይቶ ለማጥፋት ዘምቶ እንደነበርና የተሓህት/ወያነ እንደመከተው ያምናሉ፤ ይህንንም ደግፈው ይሞግታሉ። እስከ ምጽአተ-ተሓህት/ወያነ ድረስ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች

ተነጥሎና ሆን ተብሎ ትግራይ ብቻ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መብቶቹ እንዲገፈፍ ተደርጎ ነበር ብለው ያምናሉ። ይህ በጣም የተሳሳተ አመለካከትና ድምዳሜ ቢሆንም በአገዛዙ እመቃ ምክንያት ሌሎች ወገኖች እውነተኛውን ታሪክ ማቅረብ በማይችሉባትና እውነተኛውን ታሪክ ለማወቅ ዕድሉ በማይገኝበት ትግራይ ውስጥ ሆነው የሚያርሙት አይሆንም።

በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ አገዛዙ የተከላቸው አማኬላዎችም የባንዳ ተልዕኰአቸውን ለመወጣት የእብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል እንዲሉ በትግራይ ሕዝብ ስነ-ልቦና ውስጥ ጥርጣሬ የሚፈጠር አርቲ ቡርቲ በመንዛት የሕዝቡን አንድነት ለማዳከምና የኅብረት ትግሉን ለማሰናከል ምክንያት ሆነዋል። የኤርትራና የሌሎች የብዙ አካባቢዎች ሁኔታም ከዚህ ብዙ የተለየ አይደለም። በዚህ ምክንያት ነው እውነተኛ ታሪክን ማሳወቅ፣ ሕዝቡ ወዳጅና ጠላቱን እንዲለይ ትክክለኛ ዕውቀት መስጨበጥና ትክክለኛ መረጃ ማስነቅ የማንኛውም የሕዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ዋነኛ ተልዕኰና ከግዳኞቹ አንደኛው የሚሆነው።

ወዳጅና ጠላትን በመለየቱ ሥራ ውስጥ የአገዛዙ እስትንፋስ የሆነው ፋሺስቱ ተሓህት/ወያነ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የነበረውን፣ ያለውንና ሊኖረው የሚችለውን ግንኙነት በሚገባ መፈተሽ ቀዳሚው ሥፍራ መያዝ ያለበት ጥያቄ ነው። ይህንንም ሁኔታ በሚገባ ለመረዳት "የተሓህት/ወያነ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭና ተቆርቋሪ ነውን? የትግራይ ሕዝብ ከመሰረቱ ጀምሮ የተሓህት/ወያነን ዓላማ ደግፎና በእርሱ ተመርቶ ተንቀሳቅሷልን? እውን የተሓህት/ወያነ ታላቅ ትግራይን ለመመስረት ነው የታገለው? ሁሉንም የትግራይ አካባቢዎችንና ተወላጆችንስ በዕኩል ዓይን ይመለከታልን?" የመሳሰሉ ጥያቄዎችን አንስቶ መወያየት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የቀድሞ የተሓህት/ወያነና የኢህአዴግ ፖሊት-ቢሮ አባልና የተሓህት/ወያነ ትግራይ ክልል አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ገብሩ አሥራት የጻፉት መጽሓፍ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው።

የአቶ ገብሩ መጽሓፍ የተሓህት/ወያነን ክንብንብ በከፊል ገልጦ እውነተኛ ማንነቱና ተግባሩ ያሳየ የውስጥ አዋቂ ምስክርነት ነው። የድርጅቱና የትግራይ ሕዝብ ግንኙነት ባህሪይንም ያሳየ ነው። ድርጅቱና የአመራሩ አባላት በሕዝቡ ላይ የፈጸሙት ወንጀልና ክህደትንም በተወሰነ ደረጃ እርቃን ያወጣ ነው። ለዚህም ነው አቶ አበበ ተክለ-ኃይማኖትን (ጆቤን)፣ ዶ/ር አዲስ-ዓለም ባሌማን፣ አቶ ስብሓት ነጋን ጨምሮ ብዙ የድርጅቱ አመራር አባላት፣ አመራር-ነበር ግለሰቦች፣ አባላትና ጋሻ ጃግሬዎችን ያንጨረጨረው። እንደ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ዕምነት የአቶ ገብሩ ሥራ የዚህን መሰሪ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር ድርጅት ወንጀሎችንና የአገር ክዳትን ተግባራት በማጋለጥ ረገድ ያበረከተው አስተውጽዖ እጅግ ከፍተኛ ነው። ያም ሆኖ ግን ገና ብዙ መገለጥ የሚገባቸው ያልተጋለጡ ድርጅቱን የሚመለከቱ ጉዳዮች አሉ። ስለዚህ አቶ ገብሩ ገና የሚያስነብቡን የሚያሳውቁን ምስጢርና ቁም ነገር ይኖራል ብየ አምናለሁ። ይህ ማለት ግን ይህንን ማድረግ የአቶ ገብሩ አሥራት ብቻ ኃላፊነትና ሥራ ነው ማለት አይደለም።

ይልቁንስ እንደ አቶ ገብሩ ያለ እውነቱን የመረጠና ቁርጠኛ አቋም ያያዘ ሰው ሊያደርገው የሚገባ ጉዳይ ነው። አፋችሁ ተለጉሞ ያለው ካፈርኩ አይመልሰኝን የመረጣችሁት የድርጅቱ አመራር ነበሮችም የአቶ ገብሩን ፈለግ ተከትላችሁ ከእውነት ጋር እንድትታረቁና እውነቱን እንድትገልጡ ይጠበቅባችኋል።

በመግቢያው እንደተገለጸው የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የሚታዬውን ወዳጅና ጠላት የመለየት ብዥታን ለማጥራት ለሚደረገው ጥረት አስተዋፅዖ ለማድረግ ነው። ስለዚህ ከዚህ በላይ በጥያቄ መልክ በተነሱት ነጥቦች ዙርያ በውሱን ደረጃ በመወያዬት የትግራይ ሕዝብና የተሓህት/ወያነ ግንኙነትን ለማሳየት ይሞክራል።


- **ተሓህት/ወያነ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭና ጥቅም አስከባሪ ነውን? የትግራይ ሕዝብ ከመሰረቱ ጀምሮ የተሓህት/ወያነን ዓላማ ደግፎና በእርሱ ተመርቶ ተንቀሳቅሷልን?**

ታሪክ አበክሮ እንደሚመሰክረው የክልሉ መስፋትና መጥበብ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ትግራይ የጥንታዊት ኢትዮጵያ መንግሥትነት ማዕከል የነበረው ክልል ውስጥ የሚገኝ ክፍለ-ሀገር ነው። የክፍለ-ሀገሩ ህዝቡ ከሌሎች ወገኖቹ ጋር ሆኖ ለኢትዮጵያውነቱና ለአገሩ ሉዓላዊነት የከፈለው ዋጋም ታሪክ የመዘገበው ነው። የትግራይ ሕዝብ በአለፈው ታሪኩ የኢትዮጵያዊነት ማዕከል እንደሆነ የሚያምን፣ ከጥንት ጀምሮ ለአገሪቱ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት መከበር የላቀ ዋጋ እየከፈለ የኖረና ምን ጊዜ ቢሆን ኢትዮጵያዊነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶ የማያውቅ ሕዝብ ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያ ሲል እስከ የኢሠፓ/ኢህዴሪ ውድቀት ድረስ የነበረችዋን ኢትዮጵያን ነው፤ ከአክሱም ዘመን ጀምሮ የግዛት ክልልዋ አንዳንዴ እየሰፋና ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰብሰብ እያለ የዘለቀችውን ኢትዮጵያን ነው (የአሁኑ የመን ደቡባዊ አርቢያን እስከማጠቃለል የደረሰበት ወቅት ልብ ይለዋል)፤ እስከ ጣልያን ወረራ ጊዜና በኋላም በተሓህት/ወያነ አለቃ በአቶ መለስ ዜናዊ ፊርማ እስከተገነጠለ ድረስ ፈፅሞ ከእጇ ወጥቶ የማያቀውን የኤርትራ አብላአጫ ክፍልና የቀይ ባህር በሮችዋን የምታጠቅልለው ኢትዮጵያን ነው። አሁን በጐሳ-በቀሉ ፋሺስታዊ ቡድን እየተሸራረፈች ያለችውን ማለቱ ሆኖ አያውቅም።

ተሓህት/ወያነ በተቃራኒው ከመነሻው ጀምሮ የኢትዮጵያን ታሪክ የካደና የአማራው ገዢ መደብ ምሁራን ተረት-ትረት ብሎ የደመደመ ነው። የዘመናት ታሪኳንና የግዛት አንድነትዋን የመቶ ዓመት ታሪክና ክስተት አድርጐ የፈረጀ ነው። የግዛት ሉዓላዊነትዋን ተፃርሮ ከዋነኛ ታሪካዊ ክፍሎችዋ ውስጥ አንዱ የሆነውን የኤርትራን ክልል ለማስገንጠል ከማንኛውም ኤርትራዊ ነኝ ባይ ተገንጣይ ኃይል በላይ የጣረና የተገበረ ነው። በዓለም ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ የራስን አገር የመጥላት ስሜትና የመጉዳት ተግባር ተሰማርቶ አገሪቱን የባህር በሮችዋን ያሳጣ ከሀዲ ቡድን ነው። ይህ የተሓህት/ወያነ ተግባር የብዙዎች የትግራይ-ትግርኝ ተወላጅ የሆኑ እንደነ አፄ ዮሓንስ፣ ራስ አሉላ አባ-ነጋ፣ ዘርዓይ ደረስ፣ ራስ መንገሻ

ዮሓንስ፤ በኋላም እነ ደጃዝማች በየነ ባራኺ፣ ቢትወደድ አስፋሓ ወልደ-ሚካኤል፣ መልአከ-ሠላም ዲሜጥሮስ ገብረ-ማርያም፣ ብ/ጄነራል ተድላ ዕቁቢት፣ ሼኽ ሱሌማን ኤልዲን፣ ወዘተ ወዘተ … የመሳሰሉት ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን መስዋእትነትና ገድል ያረከሰ፣ ታሪካቸውንም የፋቀ የክህደት ተግባር ነው። ይህ ድርጅት የካደው፣ ያጐደፈውና የቀለበሰው የቀደምቶቹ ኢትዮጵያዊያን የክልሉ ተወላጆች የተጋድሎ ታሪክና ሥራ ብቻ አይደለም። እርሱ ዓላማዬ ነው ብሎ እንደሚወሽከተው ሳይሆን በእውነተኛ መንፈስ የመላ ሕዝቧ ዴሞክራሲያዊ መብት የተከበርባት፣ ፍትህና ርትዕ የሰፈኑባትና አንድነትዋ የተከበረች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ብለው የታገሉ፤ እንደርሱው ሁሉ ወታደራዊውን አገዛዝ ሲፋለሙ የነበሩትንም የክልሉ ተወላጆችን ያካተቱ ድርጅቶችንም በስውር ለደርግ ያጋለጠ፣ የወጋና ቀን ጐድሎባቸው በእጁ የወደቁትንም ሕይወት በግፍ የቀጠፈ ነው። በኢሕኣፓና በኢድኅ ላይ የፈጸመው አረመኔአዊ የወንጀል ተግባር ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ እምነትና የተሓህት/ወያነ እምነት በፍጹም የማይታረቁ መሰረታዊ ልዩነት ያላቸው እምነቶች ናቸው። የትግራይ ሕዝብ ቀርቶ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የድርጅቱ አባላት የነበሩት በኢትዮጵያዊነታቸው ጥርጥር ያልነበራቸው ቁጥራቸው የማይናቅ አባላቱም ቢሆኑ የድርጅቱን ፀረ-ኢትዮጵያ አቋምን አክርረው ታቃውመዋል። እነዚህ በአብዛኛው የምዕራብ ትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ የድርጅቱ አባላት ዓላማቸው የብሔር ዕኩልነትን ማረጋገጥ እንጂ አገራቸውን መገነጣጠል አልነበረም። ስለዚህም የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው የሚለውና ትግራይን ገንጥሎ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም የሚለውን በነ አቶ ስብሓት ነጋ፣ አቶ መለስ ዜናዊ ፣ አቶ አባይ ፀሓዬ፣ አቶ ስዩም መስፍንና መሰሎቻቸው ሲቀነቀን የነበረውን ዓላማ አውግዘው ታግለዋል። ሕዝቡና ኢትዮጵያዊ አቋም የነበራቸው በርካታ ከመላው ትግራይ የሚወለዱ የድርጅቱ አባላት የነበሩት እነ አቶ ስብሓት፣ አቶ አባይና አቶ መለስ በነደፉላቸው የትልቅ ትግራይ ህልምም አልተደለሉም (**ካርታ ቁ. 1**)። እንደነ አቶ ግደይ ዘርአ-ጽዮን የመሰሉቱ ኤርትራዊ የትውልድ ሀረግ ያላቸውም ይህንን ትግራይንና ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ ተቃውመዋል።



ተሓህት/ወያነ ከውስጥና ከውጭ፤ ከሰፊው የትግራይ ሕዝብና ከአባሎች በደረሰበት ተቃውሞ ትግራይን ገንጥሎ ሪፑብሊክ የመመስረት አቋሙን አለዝቦ ቀጥሏል። ከጡት አባቱ ከኤርትራው ገንጣይ ቡድን ሻዕቢያ በደረሰበት ጫና ሳቢያ እንደሆነ በሚታመን ምክንያትም የመጀመሪያ ካርታውን ለውጦ፤ ከመርሳ ፋጡማ እስከ ጁቡቲ ጠረፍ ያለውን የአፋር ክልል የሆነውን የኤርትራ ከፍለ-ሀገር አውራጃ (በሻዕቢያ ደቡባዊ ቀይ ባህር የተሰኘው ክፍል) አስቀርቶ አዲስ ካርታ ነድፎ ሥልጣን እስከያዘበት ወቅት ድረስ ዘልቋል (**ካርታ ቁ. 2**)። የሆነ ሆኖ ግን ሁሉም ይህንንን ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት ዓላማን የተቃወሙ የድርጅቱ አባላት በተለያዩ ሰበቦችና መንገዶች ለነ ስብሓት-መለስ እርድ ተዳርገዋል።

**ካርታ ቁ. 2**
**ከ*People's Voice. Publication of the Tigray People's Liberation Front, Vol. 12, No. 1 & 2. January – June 1990* የተወሰደ ነው።**




**• Location. Tigray is situated in the northern part of Ethiopia. On the north and east, it is bounded by Eritrea; on the south by Wello and southwest by Gondor regions; and on the west by Sudan**

ሌሎች የድርጅቱ አባል ያልሆኑ የትግራይ ተወላጆችም ከዚህ የድርጅቱ ፀረ-ኢትዮጵያ ፋሺስታዊ ጥቃት አላመለጡም። ድርጅቱ የመንግሥት ሥልጣንን ከተቆጣጠረ በኋላ እንኳን ይህንን ፋሺስታዊ የውንብድና ተግባሩን አላቋረጠም። ለዚህም ባዶ ስድስት የተባለ እስር-ቤቱን ከመሃል ትግራይ ከወርዒ አካባቢ (?) ወደ መቀሌ ሲያዛውር የረሸናቸው ከአምስት መቶ በላይ በአብዛኛው የከፍለ-ሀገሩ ተወላጆች የሆኑ ኢትዮጵያዊያንንን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል። ይህ ውሳኔ በአቶ መለስ ዜናዊና በአቶ ስብሓት ተፅዕኖ የተፈፀመ ሲሆን የአብዛኛዎቹን የድርጅቱ አመራር አባላት ይሁንታ ያገኘ ነው። ይህ ጭፍጨፋ ከተካሄደባቸው ወገኖቻችን ጋር ታስረው የነበሩ አንዳንድ ወገኖች ዛሬም በሕይወት አሉ። እነዚህ በዚህ ሁኔታ በግፍ የተገደሉ ሰዎች በየአውደ-ውጊያውና ሌሎች ተያያዥ ሁኔታዎች በዚህ ፋሺስት ድርጅት እጅ የወደቁት ሰዎች ፍርድ-ቤት አቅርቦ ከፍተኛ ቅጣት ለማስወሰን በቂ ምክንያት ያልተገኘባቸው የድርጅቱ ጠንካራ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና ነበር አባላት ይገኙባቸዋል። ድርጊቱ የተፈፀመበት ወቅት ድርጅቱ ተሓህት/ወያነ አገሪቱን ከመግዛት የሚያግደውና የሚያሰጋው ነገር እንደሌለ ግልጽ የሆነበት ወቅት ነበር። ድርጊቱ የጥቂት የድርጅቱ መሪዎች የቂም በቀል ጥማት ከማርካት በቀር ሌላ አመክንዮ ሊሰጠው የሚችል አይደለም።

የትግራይ ሕዝብ የተሓህትን/ወያነ አረመኔአዊ ተግባር ገና ከማለዳው ጀምሮ ያውቀዋል፤ የድርጅቱን ፀረ-ኢትዮጵያ መሰሪ ዓላማ በመቃወሙ ሳቢያ የዚህ ፋሺስታዊ ስብስብ ጥቃት ማሚሻ የሆነው እሱ ነበርና። የትግራይ ሕዝብ ተቃውሞ ወደ ትጥቅ ትግል አድጎም በተለያዩ የአካባቢ ሕዝባዊ ሠራዊቶችና ፀረ-ጉሬላ ስብስቦች ታቅፎም ይህንን የባዕድ ተልዕኮ ፈጻሚና አስፈጻሚ ፀረ-አንድነት ጐሳ-በቀል ድርጅትን ወግቷል፤ አሳድዷል። ለአብነት ያህል በእንደርታ የዘንዶ፣ በራያና አዘቦ አዞ "ሀ"፣ በተምቤን ተኩላ፣ በኽልተ-አውላዕሎ ሽላ [?]፣ በሚል ስያሜ ይጠሩ የነበሩትን ከሁሉም የብረተሰብ ክፍል የተውጣጡትን ፀረ-ሽማቂ ህዝባዊ ኃይሎች መጥቀስ ይቻላል። ይህንን እውነታ በተሳሳተና አሉታዊ ወይም አጥቋሪ አቀራረብ ቢሆንም የተለያዩ ፀሓፊዎችም ነካክተዉታል (ለምሳሌ፥ Aregawi, 2009; Gebru Tareke, 2009)። ከእነዚህ ኃይሎች ሌላ በሁሉም ከገበሬው ክፍል ተውጣጥተው የታጠቁ ህዝባዊ ሠራዊት በመባል የሚታወቁ ኃይሎች ከሚሊሻውና ከመደበኛው የአገሪቱ ሠራዊት ጐን በቋሚነት ተሰልፈው የሚያኰራ ተግባር ፈጽመዋል። በተለይ ደግሞ እስከ 1979/80 ድረስ ተሓህት/ወያነ የረባ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተፅእኖ (influence) ባላሳደርባቸው በእንደርታ፣ በራያና አዘቦ፣ በኽልተ አውላዕሎ፣ በዓጋመና በተምቤን ደጋው ክፍል አውራጃዎች የነበሩ ህዝባዊ ሠራዊቶች ይፈጽሙት የነበረው አስተዋፅዖ እጅግ የጐላና የገዘፈ ነበር። በወረዳ ደረጃ ተፈናቃይ የነበሩት የገርዓልታ ወረዳ፣ የዋዕረብና ሰሓርቲ አካባቢ ወረዳዎች፤ በአብዛኛው ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ሥር የነበሩ የህንጣሎ፣ የድድባና-ደርጋዓጀን፣ የዋጅራት፣ የእንዳ-መኾኒ፣ የሓውዜን፣ የአጽቢ፣ የስንቃጣ፣ የእንትጮ፣ የሰለኽለኻ

[?] እና ሌሎች የዘነጋኋቸው ወረዳዎች ሕዝባዊ ሠራዊቶች ያደረጉት ገድልና እንዴት ተሓህት/ወያነን ያንቆራጥጡ እንደነበር በአካባቢው የነበሩ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት የሚመሰክሩለትና ሃቅ ነው። **ይህ የአገሪቱ ታሪክ ከቀበሌ ጀምሮ እንዲጠና በተደረገው ሙከራ መሠረት የትግራይ ታሪክ ሲጠና ተካትቶ ተጠንቷል። የጥናቱ ቅጅ ያላችሁ ለብርሃን ብታበቁት የሚስመሰግን ተግባር ነው።**

እስከ 1970ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ ድረስ ተሓህት/ወያነ በአብዛኛው ከምዕራባዊው የትግራይ ክልልና ከተምቤን ቆላማ አካባቢዎች ያለፈ የጐላ ተቀባይነትም ሆነ ተፅዕኖ ሳይኖረው ቆይቷል። እንዲህ ሊሆን የቻለው በዋናነት ድርጅቱ ይዞ በተነሳው ትግራይን የመገንጠል ዓላማና ኤርትራ ቅኝ ግዛት እንጂ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም የሚለው አቋሙ ምክንያት ነበር። ይህ የድርጅቱ የኢትዮጵያ አንድነትን የሚፃረር አቋም በሁሉም የትግራይ ክፍሎች ተቀባይነት ያልነበረው ቢሆንም በበለጠ ደግሞ በራያ፣ በዓጋመ፣ በእንደርታ፣ በኽልተ-ኣውላዕሎና በተምቤን አካባቢዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ፈጥሮበታል።

አቶ ገብሩ በመጽሐፋቸው በትግራይ ውስጥ የነበረውን የተሓህት/ወያነ ተቃዋሚ ”ደርግ በሹመትና በጥቅም አባብሎ ያገኘውን የተወሰነ ድጋፍ” በማለት ገልጸዉታል (ገብሩ፣ 2006፣ ገፅ 161)። እውነቱ ግን በከተሞችና አነስ ባለ ደረጃም ቢሆን በገጠርም በተካሄደው የፖለቲካ ሥራ የተሓህት ፀረ-ኢትዮጵያዊነት አጀንዳና እውነተኛ ማንነት በመጋለጡ ምክንያት የተፈጠረ ነው። በወቅቱ ተሓህትን ይቃወም የነበረው ወገን ድርጅቱን የተቃወመበት ዋነኛ ምክንያት ይህ እንደነበረ አንድ ተሓህት ሊመለምለው ሞክሮ የነበረ ሰው የሰጠው መልስ ብለው እራሳቸው አቶ ገብሩ በጠቀሱት ውስጥም ተመልክቷል (ገብሩ፣ 2006፣ ገፅ 158)። የወቅቱን የድርጅቱ ዓቋም የተቃወሙት በሜዳ የነበሩ የድርጅቱ አባላትም ጭምር ነበሩ። ለዚህም ነበር በወቅቱ በርካታ አባሎቹ ድርጅቱን እየኰነኑ ጥለዉት የወጡት፣ ከመንግሥት ጐን የተሰለፉት፣ ወደ ውጭ የኰበለሉት፤ መጥፎ ዕድል ገጥሟቸው ድርጅቱ ከረሸናቸው በቀር። አቶ ገብሩ የደርግን እና የኢሠፓአኮ/ኢሠፓ መንግሥትና ባለሥልጣኖቹ እንዲሁም በሥርዓቱ ያገለገሉ ሰዎችን፣ በወቅቱ የነበረው የኃይል አሰላለፍን፣ የኢሠፓ ሥርዓት ሊፈርስ ስለቻለበት ምክንያት አስመልክቶ ያላቸው አመለካከት ስሜታዊነት ያጠላበት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ይህ ጉዳይ ራሱ የቻለ የመወያያ ርዕስና የታሪክ ኩነት ስለሆነና የዚህ ጽሑፍ ዓላማም የአቶ ገብሩን መጽሓፍ መገምገም ወይም መተቸት ባለመሆኑ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ።

የመጀመሪያው ፀረ-ዐፄ ኃይለ-ሥላሴ መንግሥት አቋም የነበረው የ1934 ዓ.ም. የወያነ አመጽ የተቀሰቀሰው በእንደርታ አውራጃ ውስጥ ድድባና-ደርጋ ዓጀንና ዋጀራት ወረዳዎች ውስጥ ሆኖ የመላው እንደርታ፣ የራያና የከፊል ኽልተ-ኣውላዕሎ ገበሬዎች ያካሄዱት አመፅ ነበር። እያደር የተምቤን ገበሬዎችም በከፊል ተቀላቅለዉታል። የዚህ አመፅ ዓላማ በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ በራሱ ደንብና ራሱ በመረጣቸው መተዳደርና የፊውዳላዊው ሥርዓት ገዢ መደብ አባላትንና ሹሞችን

ማስወገድ ነበር። የአመፁ ዋነኛ መነስኤ ከጣሊያን ሙሉ ሽንፈት በኋላ በሕዝቡ ላይ የተጣለው ፈጽሞ ከአቅሙ በላይ የሆነና ሊሸከመው የማይችል የግብር ክፍያ ነበር። ሕዝቡ በሠላማዊ መንገድ ቅሬታውን ቢገልጽም ሰሚ በማጣቱና ለአስገዳጅ የመንግሥት እርምጃ በመዳረጉ መፍትሄው ኢ-ፍትሃዊ አስተዳደሩን በትጥቅ መክቶ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አድርጐ ወሰደ። ከጅምሩ ኢኰኖሚያዊ ይዘት የነበረው እንቅስቃሴ መልኩን ለውጦ የፖለቲካ መልክ ይዞ፤ ነገድ ሳይለይ ፀረ-መሳፍንታዊው አገዛዝ ትግል ሆኖ አረፈው። የፊውዳሉ መንግሥት ለዚህ የሕዝብ አመጽ ፖለቲካዊና ሠላማዊ መፍትሄ በመስጠት ፈንታ በእንግሊዝ ወታደራዊ ኃይል ጭምር በመታገዝ በጦር ኃይል ደፈጠጠው። የ1933ቱ የከፊል ትግራይ ወያነ (አመጽ) በኋላ ተሓህት/ወያነ ይዞት ከተነሳው ዓላማ ጋር ፍጹም ተጻራሪ ነው። መሠረታዊ ልዩነታቸውን እንደሚከተለው ማነጻጸር ይቻላል፥

| **የ1933 ዓ.ም. የትግራይ ገበሬዎች ወያነ** | **የተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተሓህት) በኋላ ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) አብዮት** |
|---|---|
| በኢትዮጵያዊነት ያምናል። | በኢትዮጵያዊነት አያምንም። |
| ፍትህን ለማግኘት አልሞ የተነሳ፣ በኢትዮጵያዊነት ማእቀፍ ውስጥ ራሱ በመረጣቸው ሰዎች ለመተዳደር ያቀደ ነበር። | ትግራይን ከኢትዮጵያ በመገንጠል ራስዋን የቻለች መንግሥት ለማድረግ አልሞ የተነሳ ነው። ከዚህም በላይ ኤርትራንም በማስገንጠል (በመገንጠል ማለቱ የተሻለ ይገልጸዋል) ኢትዮጵያን የባህር በሮቿን ለማሳጣት ቆርጦ የተነሳና የተገበረም ነው። |
| አርማው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነበር። | የራሱ የሆነ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ምንም ግኑኝነት የሌለው አርማ አለው። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ተራ ጨርቅ ነው ብሎ ያንቋሸሸና ጥላቻውን የገለጠ ድርጅት ነው። |

ከ1970ዎቹ የመጀመሪያው አጋማሽ ጀምሮ እነዚህ ሁለት በትግራይ ውስጥ የተካሄዱ አመጾች ቀዳማይ ወያነ እና ኻልኣይ ወያነ (የመጀመሪያው ወያነ እና ሁለተኛው ወያነ) የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸው ይገኛል፤ ወይም ተሰኝተዋል። የዚህ ስያሜ ምንጩ ተሓህት/ወያነ ቢሆንም ይሁነኝ ተብሎ በፖለቲካ ዓላማና በየዋኅ-ልምድ ተዘውትሮ በመነገሩ ሥር የሰደደ ስያሜ ለመሆን በቅቷል። ዳሩ ግን የ1930ዎቹ የትግራይ ገበሬዎች አመጽና የተሓህት አመጽ ታሪካዊም ሆነ ፖለቲካዊ ይዘቱ ሲመዘን ባለው መሠረታዊ ተቃርኖ ምክንያት ተሓህትን “ወያነ” ብሎ መጥራት ስህተት ነው። ወያነ ማለት የግዕዝ ውርስ ቃል እርባታ ሆኖ አመጽ ወይም አብዮት ማለት ነው። እንዲያ በመሆኑም ማንም አብዮታዊ ነኝ ያለ ሁሉ ሊጠራበት ካማረው የሚከለክለው ነገር አይኖርም። ተሓህት ግን ወያነ ሲል የመጀመሪያ ወያነ እና ሁለተኛው ወያነ (ቀዳምይ ወያነ፣ ኻልኣይ ወያነ) በሚል መንፈስና አጠራር ሲሆን የመጀመሪያው ወያነ ትግል ወራሽ ለማለት ነው፤ ይህንን አስተጋብታ Jenny Hamond “Fair From The Ashes”

እንዳለችው ዓይነት (Hammond, 1999)። ስለዚህ ይህንን ጐሳ-በቀል ፋሺስታዊ ስብስብን ወያነ ብሎ መጥራት የሌለበትን ተፈጥሮ ሰጥቶ ለፍትህና ርትዕ የቆመ ኢትዮጵያዊ ኃይል ማድረግ ነው የሚሆነው።


በመሰረቱ ድርጅቱ ሲነሳ ራሱን ወያነ ብሎ አልሰየመም። የተደላደለ የድርጅት መልክ ይዞ ሲወጣ ለራሱ የሰጠው የትግርኛ መጠሪያ ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተ.ሓ.ህ.ት.) የሚል ነው። በእንግሊዝኛው ስያሜው EPLF (***Eritrean*** People's Liberation Front) የሚለውን መጠርያ ገልብጦና **'E'**ን በ**'T'** ተክቶ TPLF (***Tigray*** People's Liberation Front፣ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት/ግንባር) የሚል ነበር። "የትግራይ" የሚለው ስያሜ ደግሞ ቀደም ብሎ በነበረው አመለካካከትና ልምድ ትግራይ ማለት ከወርዒ ወንዝ ማለትም ምዕራባዊው የትግራይ ክፍል አድርጐ ይመለከት በነበረው የመሃል፣ ደቡብና ሰሜናዊ የትግራይ ክፍል ሕዝብ፤ በዋናነት ደግሞ ተሓህት/ወያነ አቶኩሮበት በነበረው የገጠሩ የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ በየእኛነት እንዲታይ አላስቻለውም። ከዚህ በላይ ደግሞ ድርጅቱ በአብላጫው በአክሱም፣ ሽሬ እና ዓድዋ ተወላጆች የተሞላና የሚመራ ከመሆኑም በላይ ይበልጥ ያተኰረውም በነዚህ ሦስት አውራጃዎች ስለነበር ከሌላው የክፍለ-ሀገሩ ክልል ጋር እዚህ ግባ የሚባል ትስስር አልነበረውም። አሁንም በግልጽ እንደሚታየው የአክሱም፣ ሽሬና ዓድዋ (አሽዓ) እና የኤርትራ ተወላጆች (ግማሽ ወይም ሙሉ) የበላይነት እንዳለ ቀጥሎ እና ይበልጥ ጠቦ እስከዛሬ ዘልቋል። ሌላው አድርባይ አጃቢ ነው። አሽዓ ማለት በድርጅቱ የገነነ አውራጃዊ ክፍፍል ተከስቶ በነበረበት ድርጅቱ ሕንፍሽፍሽ እያለ በሚጠራው ወቅት የሦስቱ አውራጃዎች ተወላጆች መለያ ተደርጐ ተወስዶ የነበረ ነው።

በመጀመሪያ የድርጅቱ ዓመታት አብላጫና ቁልፍ መሪዎቹ የነበሩት የአሽዓ ተወላጆችና ኤርትራዊያን የድርጅቱን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባህርይ፣ የኤርትራ ግንጠላ አጀንዳ አራማጅነት እና ጠባብ-ብሄረኛነቱን የኰነኑትን የሌላ አውራጃዎች ተወላጆችንንና ተመሳሳይ አመለካከት ያንጸባረቁትን ጥቂት የአሽዓ ተወላጆችንም በግፍ የፈጁ ለመሆናቸው የአደባባይ ምስጢርና ድርጅቱም ስህተቱን አምኖ ይቅርታ ያልጠየቀበት አስቀያሚ ጠባሳው ነው። ከዚህም በላይ የድርጁትን አቋም ጥያቄ ውስጥ ያስገቡና የተቃወሙ፤ እንዲደግፉት ተጠይቀው ፈቃደኛ ያልሆኑ፣ የሌላ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ ናቸው ብሎ የፈረጃቸው፣ በአገሬው ባህል መሠረት በአዛውንትነታቸውና በጐልማሳነታቸው መክረው የሚያሰሙ የመሰላቸው፣ ... ወዘተ የክፍለ-ሀገሩ ተወላጆችንም ያለ ርህራሄ አጥፍቷል።

ድርጅቱ ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተ.ሓ.ህ.ት.) የሚለውን መጠሪያውን አውልቆ ህዝባዊ <u>ወያነ</u> ሓርነት ትግራይ (ህ.ወ.ሓ.ት.) የሚል ጭምብል ያጠለቀው ከተመሰረተ ከበርካታ ዓመታት በኋላ በ1970ዎቹ ነበር። ይህ ያደረገበት መሠረታዊ ምክንያትም ከ1933ቱ ወያነ ማለትም የመሃልና የደቡብ ትግራይ ሕዝብ ፍትሃዊ ትግል ጋር ትስስር ለመፍጠርና እራሱን የዚሁ ትግል ወራሽ አድርጐ ለማቅረብ

ነው (ካርታ ቁ. 3)። ተሓህት ሥሙን ቀይሮ ወያነ ሲሰኝ መሰረታዊ ፀረ-እትዮጵያ አንድነት እምነቱን ግን ፈፅሞ አልቀየረም። ይህንንም ኤርትራን በማስገንጠል (በመገንጠል!) በወሰደው አቋምና ወደፊት ኢትዮጵያ ተበጣጥሳ በጥቃቅን የጐሳ መንግሥታት ትትካ ዘንድ የክልል ሰንደቅ ዓላማ፣ የመንግሥትነት ቅርጽ የያዙ አካባቢያዊ ጐሳና ነገድ መሰረት ያደረጉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች፣ ወዘተ በመፍጠርና በማደራጀት በሚፈጽመው ደባ እያረጋገጠ ነው። ኤርትራ ራስዋን የቻለች አገር ነበረች ለሚለው ክርክር ከሚቀርቡት መሚገቻ ውስጥ የራስዋ ፓርላማ ነበራት፣ የራስዋ ሰንደቅ ዓላማ ነበራት የሚለው በዋናነት መቅረቡ ትምህርት ሰጭ ሊሆን ይገባው ነበር።

አንዳንድ የዋኅን አቶ መለስ ዜናዊ ማለም ትችላላችሁ ብለው በፈቀዱላቸው መሠረት "ተሓህት/ወያነ አሁን አቋሙን ለውጦ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እየሰራ ነው፣ ዓባይን እየገደበ ነው፣ ምንትስ፣ ምንትስ" እያሉ ህልማቸውን ቢቀጩም "ድመት መንኩሳ፤ ያባትዋን አትረሳ" ነውና ቢሂሉ፤ ተሓህት/ወያነ ግን ሥራውን አይተውም። እነዚህ ወገኖች ነገ ዓባይ ተገድቦ ሲያበቃ "ዓባይ ለሶማሊ፣ ለአፋር፣ ለአማራ፣ ለጉራጌ፣ ... ወዘተ ምኑ ነው" እንደማይባል ሊያረጋግጡልን የሚችሉበት አስረጅና መላምት የለም።




የተሓህት/ወያነ ከምዕራባዊው የትግራይ ክልልና ከተምቤን ቆላማ አካባቢዎች ያለፈ የጐላ ተቀባይነትም ሆነ ተፅዕኖ ሳይኖረው እስከ 1970ቹ አጋማሽ ድረስ ለመዝለቁ ሌላም ተጨማሪ ምክንያት ነበረው።

የኢህኣፓ (EPRP) ሠፈሩን በዓጋመ መቆርቆርና በዓጋመና በተምቤን አካባቢ ፈጥሮት የነበረው ተቀባይነትና በልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ይመራ የነበረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረትም (EDU) በመካከለኛው ሰሜናውና ደቡባዊ ትግራይ የነበረውም ፖለቲካዊ ተጽዕኖም ለተሓህት/ወያነ በካባቢው እምብዛም ተቀባይነት ያለማግኘት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ነበረው።

በአጠቃላይ እላይ በተዘረዘሩት የተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ተሓህት/ወያነ በአብዛኛው ከምዕራባዊው የትግራይ ክልልና ከተምቤን ቆላማ አካባቢዎች ያለፈ እምብዛም የጐላ ተቀባይነትም ሆነ ተፅዕኖ ሳይኖረው እንዲቆይ ተገዷል። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የትግራይ ሕዝብ የማንነት እምነትና የተሓህት/ወያነ እምነት ፈጽሞ የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ነበሩ። በዚህ ሳቢያ የትግራይ ሕዝብ የወያነን ዓላማ ተቃውሞ ሲታገል ቆይቷል። የወያነ ዓላማ ተሳክቶ ኤርትራ እንዳትገነጠል ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍለ-ሃገራት ሕዝብ የበለጠ፤ ቢያንስ ደግሞ እኩል የሆነ ዋጋ ሲከፍል ኖሯል። በወጣት ዘማቾች፣ በፀረ-ሽማቂ ኃይሎች፣ በሕዝባዊ ሠራዊቶች፣ ወዘተ … እየተደራጀ የሕይወት፣ የንዋይና የጉልበት መስዋዕትነት ከፍሏል። ትግራይ ከሌሎች የአገራችን ክፍል ጋር ሲነጻጸር በኢኰኖሚ ደከም ብሎ ይታይ የነበረ ክፍለ-ሀገር ቢሆንም በሶማሊያ ወረራ ወቅት ክፍለ-ሀገሮች ያደርጉት በነበረው የእናት አገር ጥሪ የኢኰኖሚ ድጋፍ መሠረት ወደ ስምንት ሚልዮን ብር በማዋጣት ከአገሪቱ ክፍለ-ሀገሮች የሁለተኛነት ሥፍራ ይዞ እንደነበር በወቅቱ በይፋ የተገለጠ ጉዳይ ነው (የበለጠው አዲስ አበባ ብቻ ይመስለኛል)። ይህንን ሁሉ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በሥራ ምክንያት በተዘዋወረባቸው የትግራይ ክፍለ-ሀገር አውራጃዎችና በኤርትራ፤ ለአብነት ያህል፤ የታዘበው እውነታ ነው።

የትግራይ ሕዝብ አቋም ፀረ-የተሓህት/ወያነ ዓቋም ከነበረ ደግሞ ይህ ድርጅት የዚህ አገሩን አፍቃሪ፣ ለአንድነቱና ለነፃነቱ ሟች ጀግና ሕዝብ ወኪልና ጥቅም አስከባሪ ሊሆን የሚችልበት ቀመር ፈጽሞ የለም። ትግራይ እኰ ሰሜን አሜሪካ ወይም ኤሺያ ወይም ሌላ ቦታ ላይ ያለ ሌላ ራሱን የቻለ አገር አይደለም፤ የኢትዮጵያ አንድ ክፍል ነው። ታዲያ በምን መለኪያ ነው ተሓህት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እየጐዳ፣ የአብዛኛው ሕዝቧን መብት እየረገጠና እያፈነ የትግራይ ሕዝብ ጥቅም አስከባሪ ሊሆን የሚችለው? እንዴት ሆኖ ነው አገሩ ያለ ባሕር በር እንዲቀር መደረጉ፣ በኢትዮጵያዊነቱ እንደልቡ ተዘዋውሮ ሠርቶ እንዳይኖር በዘር ተሸንሽኖ መገደቡ፣ በስሙ በሚቀጥፍ ዋልጌ መንደርተኛ ቡድንና የሥርዓቱ ተጠቃሚ በሆኑ ነብሰ-በላ ባለሃብቶች ዳፋ ጥርስ መግባቱ፣ … ወዘተ ጥቅሙ መከበር የሚሆነው?

የትግራይ ሕዝብ ጥቅም የሚከበረው የመላ አገሩ ጥቅም ሲከበር ነው። አገዛዙም በአንድ ወቅት ፍትሃዊም አፋኝም የሆነ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ዓይነት ተፈጥሮ ሊኖረው ፈፅሞ አይችልም። በአንድ የጊዜ

ቅጽበት ውስጥ ከሁለቱ አንዱ ብቻ ነው መሆን የሚችለው። በቀሪቱ የአገሪቱ ክፍል ውስጥ አፋኝና አረመኔአዊ የሆነው አገዛዝ እዚያው በዚያው ከመቅጽበት ለትግራይ ሕዝብ ሲሆን ፍትሃዊና የሕዝብ መብት አስጠባቂ ሊሆን አትችልም። አሜሪካዊው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ማርቲን ሉተር በወቅቱ በአገራቸው የነበረው ሁኔታ አስመልክተው "… Injustice anywhere is a threat to justice everywhere." ያሉት ይህንን ነው የሚያሳየን። በርግጥ አገዛዙ ጃስ የሚላቸው ውሾች በትግራይ ሕዝብ ሥም እያጭበረበሩ የትግራይ ሕዝብ የአገዛዙ ጭፍን ደጋፊና የሥርዓቱ ተጠቃሚ እንደሆነ አድርገው ሊያላዝኑ ይችላሉ፤ አገዛዙም እንዲያ ሊያደርግ ይችላል፤ አገዛዙ ድርጎ እየሰፈረና ፍርፋሪ እየወረወረ ያሰማራቸው ባንዳዎችም በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ መሽገው ይህንን ሊያስተጋቡ ይችላሉ። ይህ ሁሉ ግን፤ "አባ በበሉ፣ አማሆይ አገሱ" በሚል ስሌት ካልተሰላ በቀር፤ ውሸት ነው። ወይም የትግራይ ሕዝብ ማለት ላይ መግባባት የለም ማለት ነው፤ ብዥታ አለ ማለት ነው። የተሓህት/ወያነዎች ጀግኖች አባቶቻችን ሲሉ እንደነ ባንዳው የአቶ መለስ ቀድመ-አያት ባሻይ አስረስ፣ እንደነ ደጃዝማች ኃይለ-ሥላሴ ጉግሳ፣ … ወዘተ ማለታቸው፤ የነሱ ተቃዋሚ የሆኑት ደግሞ እንደነ ዐፄ ዮሐንስ፣ አሉላ አባ-ነጋ፣ ወዘተ … ማለታቸው ሆኖ እንድሚለያዩት ማለት ነው።

ሌላኛው አስገራሚ ነገር ተሓህት/ወያነ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ማለቱ ሳይሆን የዴሞክራሲያው ሥርዓት ምንነት ገብቶናል የሚሉ ኃይሎችና የዚህ ድርጅት ግትልትሎችም ጭምር እንዲያ ነው ብለው ማመናቸው ወይም መቀበላቸው፣ ወይንም ድርጅቱን መጥራታቸው ነው። ነፃ መውጣት ማለት ምንድን ማለት ነው እንዴ?! የትግራይ ሕዝብ ነፃ ሆኖ የኖረ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ነፃነት ለማስከበር ሲታገል የኖረ ሕዝብ ነው። ታዲያ ከማን ነው ነፃ የሚወጣው?! ያውም ነፃነት በማይሰማቸው የባንዳ ልጆችና የራሳቸውን ክፍለ-ሀገር አስገንጥለው ተጣብቀዉን በቀሩ መዥገሮች! ይህ በጣም አሳዛኝ አላዋቂነትና ብሽቅ ቀልድ ነው። በእርግጥ የትግራይ ሕዝብ እንደ ማንኛውም የአገሪቱ ሕዝብ በአገሪቱ የመንግሥት ሥልጣን በጨበጡ ገዥ መደቦችና አገዛዞች ሲጨቆንና ሲመዘበር የኖረ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነት ሥርዓት ተላቆ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቱ በተከበረበት ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተዳደር አለበት። ለዚህም መታገል አለበት። ይህ ደግሞ በመደባዊ ትግል እንጂ በጐሳ ፖለቲካ ሳቢያ ገዥና ተገዢን፣ በይና ተበይን በአንድነት አጉሮ በሚያንተከትክ፤ አረመኔያዊ አገዛዝን ለማስቀረት ሳይሆን በራስ ጐሳ ጅቦች ለመበላት በሚዳርግ የጐሳዎች ወይም ብሄረ-ሰቦች መገንጠል እዉን የሚሆን አይደለም። የኤርትራ ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ኃቅ ነው የሚያሳየን።

የትግራይ ሕዝብ ገና ከጥዋቱ ይህንን በተገነዘቡ የክፍለ-ሀገሩ ተወላጆች እውነታው እንዲያውቅ በመደረጉ የተሓህት/ወያነን ዓላማ ደግፎና በእርሱ ተመርቶ አልተንቀሳቀሰም። ዛሬም ቢሆን እንደማንኛውም ቀሪው የአገሪቱ ክፍል ሳይሆን በባሰ ሁኔታ ተቀፍድዶና ተሸብቦ እንጅ የዚህ

መንደርተኛ ድርጅት ተከታይ ያለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ለዚህም በምርጫ 97 የወሰደው አቋም ጉልህ አስረጅ ነው።

ከዚያ በላይ ደግሞ የዐፄው አገዛዝ ገዢ መደብን በዐፄው አገዛዝ የገዢ መደብ መሳፍንትና የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሊህቃን ልጆች መተካት እና አዲስ ነፍጠኛ ገዢ መደብ መፍጠር የትግራይን ሕዝብ ጥቅም አያስጠብቅም። ለአብነት ያህል የተምቤኑ ፊውዳል የግራዝማች አብራሃ ልጅ አቶ ስዩ አብራሃ፣ የሽሬው ፊውዳል የደጃዝማች አርኣያ ልጅ አቶ ሓየሎም አርኣያ፣ በዐፄው ዘመን የትግራይ ልማት ድርጅት ሥር-አስኪያጅና የልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ባለሟል የነበሩት የትግራይ ሕዝብን ደም የመጠጡት የሠራዬው (ኤርትራ) ተወላጅ የአቶ ገብረ-ክርስቶስ ገብረ-እግዚአብሄር (የመቀሌው Green Hotel ባለቤት) ልጆች እነ አቶ ብርሃነ ገብረ-ክርስቶስ፣ የመቀሌው ፊውዳል ነጋዴ የባላምባራስ ተክለ-ኃይማኖት ካሕሳይ ልጆች እነ አቶ አበበ ተክለ-ኃይማኖት፣ የዓድዋ መሬት ከበርቴ ፊታውራሪ ልጅ አቶ ስብሓት ነጋ፣ ወዘተረፈ … መጥቀስ ይቻላል። ትላንት አባቶቻቸው ጋጡት፤ ዛሬ ደግሞ ልጆቻቸው እየጋጡት ብቻ ሳይሆን እየቀለዱበትም ነው።

የትግራይ ሕዝብ ተሓህት/ወያነን ይቃወም ከነበረ እንዴት ሆኖ ታዲያ ተሓህት/ወያነ አሸነፈ?

**በክፍል ሁለት ይቀጥላል።**

yane.07.2006@gmail.com